2ኛ ዓመት ቁጥር 22
2nd Year No. 22

ባሕር ዳር መስከረም 30 ቀን 1990 ዓ.ም.
Bahir Dar 10th Oct. 1997

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ
ZIKRE HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE
IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

የአንዱ ዋጋ ብር 1.00	በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ተጠባባቂነት የወጣ	የፖ.ሣ.ቁ. 312 P. O. BOX

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር22 /1990
የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት አዋጅ ቁጥር 2/1988፣ አንቀጽ 80/3 እና 88/3ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ
ገጽ 2

CONTENTS

Proclamation 22/ 1997
A proclamation to amend article 80/3 and 88/3 of the constitution of the Amhara National Region
Page 2

አዋጅ ቁጥር 22/1990
የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት አዋጅ ቁጥር 2/1988፣ አንቀጽ 80/3 እና 88/3 ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

በሕግ መንግስቱ አንቀጽ 80/3 እና 88/3 ን ላይ የተደነገገው የወረዳ እንደ ሁም የቀበሌ ምክር ቤቶች የሥራ ዘመን የመረጣቸውን ህዝብ በብቃት ለማገልገል የሚያስችል ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን ገንብቶ ወደ ተግባር በማስገባት የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ከመፍጠር አኳያ አጭር በመሆኑ፣

የምርጫ ተግባር የመንግስታዊ መዋቅሩን የሕዝቡን ሰፊ ተሳትፎ የሚጠይቅ በመሆኑና ይህም በየአጭር ጊዜ መከናወኑ በሥራ፣ በበጀት ያለውን ተፅዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት የሥራ ዘመናቸውን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

Proclamation 22/ 1997
A proclamation to amend article 80/3 and 88/3 of the constitution of the Amhara National Region

Where as the Service term of the Woreda and Kebele council, stipulated under article 80/3 and 88/3 of the constitution is to short that it doesn't suffices, to facilitate the conditions for rendering the necessary, training that build their capacity of serving their nominees efficiently,

Where as it has become necessary to amend the service term of the nominees, as the act of governmental organizations and the peoples by large there by, considering that to run in such a short period of time as an adverse effect against the budget and their activities,

ሕዝቡ በመረጣቸው የወረዳ እና የቀበሌ ም/ቤት አባላት ላይ አመኔታ ባጣ ጊዜ በሕግ መሠረት ከስልጣን ሊያነሣቸው የሚችልበትን ሁኔታ በግልፅ መደንገግ ተገቢ መሆኑን በመገንዘብ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልል መንግሥት ምክር ቤት በአንቀጽ 100 ላይ የክልሉ ሕገ መንግስት ለማሻሻል፤ እንደሁም በአንቀጽ 49/3/1 ላይ ሕግ ለማውጣት በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን አውጇል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት፤ አንቀጽ 80/3 እና 88/3 ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 22/1990" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ማሻሻያ</u>

የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ - መንግስት አዋጅ ቁጥር 2 1988 80/3 እና 88/3 እንደሚከተለው ተሻሽለዋል፡፡

ሀ. የሕገ መንግስቱ፤ አንቀጽ 80/3 ተሻሽሎ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡
3. የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ ምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡

ለ. የሕገ መንግስቱ፤ አንቀጽ 88 ሥራ በተጨማሪ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 ታክሏል፡፡
4. የቀበሌ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡ የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማብቃቱ በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡

ሐ. የሕገ መንግስቱ፤ አንቀጽ 88/3 ተሻሽሎ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡
3. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሠረት ከምክር ቤቱ አባልነት ይወገዳል፡፡

መ. የሕገ መንግስቱ፤ አንቀጽ 88 ሥራ በተጨማሪ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 ታክሏል፡፡

3. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በክልሉ ም/ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር
መስከረም 30 ቀን 1990
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ምክር ቤት

Where as it has become necessary to stipulate the conditions by which the people may remove the members of Kebele and Woreda councils by law, whenever they lose their confidence on the nominees,

Now therefore, in accordance with the power to amend the constitution of the region under article of 100 and to in act laws under article 49/3/3 of the constitution, the council of the Amhara National Regional State, here by, proclaimed as follows.

1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as " proclamation to amend Article 80/3 and 88/3 no 22/ 1997 of the constitution of the Amhara National Region"

2. <u>Amendment</u>

Article 80/3 and 88/3 of proclamation no 2/ 1996/ 97 - of the constitution of the Amhara National Region, is here by amended as follows.

A. Article 80/3 of the constitution is amended and replaced by the following new sub article 3.

3. The term of office of the Woreda council shall be five years. Election shall be conducted before the termination of the term of office of the council.

B. A new sub article 4 is added under article 80 of the constitution.
4. The term of office of the council of the Kebele shall be five years. Election shall be conducted before the termination of the term of office of the council.

C. Article 88/3 of the constitution is hear by amended and replaced by following new sub article 3.

3. Any member of the council shall, in accordance with law, be removed from the membership of the council where the electoral lose confidence in him/her.

D. A new sub article 4 is added under article 80/3 of the constitution.

3. <u>Effective Date</u>

This proclamation shall come in force from the date of its ratificiation by the Council of the Region.

Done at Bahir Dar
10th day of Oct. 1997
Council of the Amhara National Regional State.

የገጽ ማተሚያ ድርጅት ታቀመ

182

182